ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን
**Ethiopian Orthodox Tewahedo Church of Our Savior**
4401 Minnehaha Avenue South ♦ Minneapolis, MN 55406, U.S.A.
Tel (612) 721-1222 ♦ **Email: dsmachurch@gmail.com**

ቀን : 05/19/2024
ቁጥር : DSMA-016/24

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን

**ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን**
**ሚኒያፖለስ, ሚኒሶታ, ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ**

## የሰባኬ ወንጌል አገልጋይ ለመቅጠር የወጣ ማስታወቂያ

የደብረ ሰላም መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን በሰሜን አሜሪካ ሜኒሶታ ግዛት ሚኒያፖለስ ከተማ የሚገኝ በግዛቱ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ሲሆን በሺዎች ለሚቆጠሩ በስደት ላሉ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ምእመናንን በርካታ መንፈሳዊ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ታላቅ ቤተክርስቲያን ነው። ከዚህ አንፃር የቤተክርስቲያናችን አገልግሎት እና የምእመናንን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ እየሰፋና እያደገ በመምጣቱ አንድ ተጨማሪ የስብከተ ወንጌል አገልጋይ መምህር መቅጠር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

### የቅጥር መስፈርቶች

1. ክህነት ያለው (የቅስና ወይንም የዲቁና ማዕረግ ያለው)
2. ከታወቀ የአንድምታ ትርጓሜ ጉባኤ ቤት የተመረቀ እና የስብከተ ወንጌል ችሎታ ያለው
3. ከአብነት ትምህርት ቤት የተመረቀ ወይንም የሥስነ መለኮት ኮሌጅ ምሩቅ የሆነ
4. በስብከተ ወንጌል አገልግሎት ቢያንስ የአምስት ዓመት ልምድ ያለው
5. ዘመናዊ ትምህርት ቢያንስ 12ኛ ክፍልን ያጠናቀቀ
6. ልጆች በማስተማር በቂ ልምድ ያለው
7. በእግሊዝኛ ቋንቋ መግባባት የሚችል እና ቢቻል በዚህ ቋንቋ ማስተማር የሚችል
8. መልካም ጠባይና ሥነ ምግባር ያለው

ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ አገልጋዮች ከታች በተጠቀሰው ድረ ገጽ ላይ የተለጠፈውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት በኢሜል ወይንም በፖስታ ወይንም በሚያውቁት ሰው በኩል ማመልከቻውን እና ማስረጃዎቻቸውን ይህ ማስታወቂያ በወጣ በ60 ቀን ውስጥ መላክ የሚችሉ መሆኑን እንገልፃለን።

ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን,
ሚኒያፖለስ, ሜኒሶታ, ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ

---

ድረ ገጽ www.debreselam.net
ኢሜል dsmachurch@gmail.com
ፖስታ 4401 Minnehaha Avenue S., Minneapolis, MN 55406, U.S.A.
ስልክ +1 (612) 721-1222